# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 47

ታህሳስ 30 ቀን 2015ዓም(08-01-2023)

የፈረንጆቹን የ2023 ዓም የመጀመሪያ ወር ከተቀበልን ስምንት ቀናት ሆኖናል፣ የአገራችንን የኢትዮጵያን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ የልደት በዓል ካከበርንም ዛሬ ሁለተኛው ቀናችን ነው።ዛሬ የታህሳስ ወር ማለቂያው ሲሆን በነገው እለት የጥር ወርን እንቀበላለን።ባለፈው ስርጭታችን የአገራችንን የታህሳስ ወር ስያሜና ትርጉሙን ማቅረባችን አይዘነጋም፤ አሁን ደግሞ የፈረንጆቹ ዓመት መግቢያ የሆነው የጃንዋሪ ወር ስያሜ እንዴት እንደመጣና ምንስ ይዞ ይመጣል ተብሎ እንደሚጠበቅበት ትንሽ ለማለት እንወዳለን።ጃንዋሪ የሚለው ስያሜ የመጣው ከሮማውያን አማልክት አንዱ በሆነው ባለሁለት ፊቱ ጃኑስ ከተባለው ጣኦት ሲሆን ሁለቱ ፊቶቹ በሁለት አቅጣጫ የሚመለከቱ ሆነው የወጣውንና የሚገባውን ማለትም ያለፈውንና የሚመጣውን ዓመት የሚያዩ ናቸው። ጃንዋሪ የዓመቱ መጀመሪያ በመሆኑ ድቅድቅ ካለው የክረምት ጨለማ ማግስት ብሩህ ቀን የመውጣቱን አቅጣጫና የተስፋ ጭላንጭል ያሳያል ተብሎ ይታመናል።እኛም ኢትዮጵያውያን የዓመቱን መጀመሪያ የመስከረምን ወር የምንገልጽበት መንገድ ተመሳሳይ ነው።በክረምት የጎርፍና ዝናም ምክንያት ተለያይቶ የከረመ ቤተሰብ የሚገናኝበት፣ከጨለማው የክረምት ጊዜ ተላቀን ብሩህ ቀን የምናይበት፣በጭቃና አሮንቃ የተዋጠ መስክ ለሰብል የሚበቃበት፣በልቶ ማደር ለሚቻልበት የበልግ ወቅት የምንሸጋገርበት በመሆኑ የመስከረም ወር ብዙ ተስፋዎች የሚጣሉበትና እቅዶች የሚነደፉበት ወር ነው።ያንንም በሚከተሉት ስንኞች እንገልጸዋለን።

መስከረም ሲጠባ አደይ ሲፈነዳ፣

እንኳን ሰው ወዳጁን ይጠይቃል ባዳ።

መስከረም ሲጠባ አይቸው ጉዴን ፣

የኑሮዬን ነገር ያከራረሜን።

አሁን የገባውን ጃንዋሪ የመሰሉ ብዙ ጃንዋሪዎችን አሳልፈናል።የአገራችንንም የመስከረም ወራቶች እንዲሁ ተቀብለን ሸኝተናል።የወራቶቹ መምጣትና መሄድ ያበረከተልንን ስንመረምረው ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ከመልካሙ ይልቅ መጥፎው ጎልቶና ገዝፎ ይገኛል።ሌሎቹን አያሌ መስከረሞች ትተን ከደርግ ወዲህ ያሳለፍናቸው መስከረሞች ቢቆጠሩ 49 መስከረሞች ይሆናሉ።በነዚያም መስከረሞች ከጥሩው ይልቅ ብዙ መጥፎ ክስተቶችን አስተናግደናል። ከ1967ዓም መግቢያ መስከረም ላይ ብንነሳ ከድጡ ወደ ማጡ፣ከሳት ወደ ረመጡ የገባንበት፣ለጨካኝ የወታደር አምባገነን ሥርዓት የተሻገርንበት፣ እስከ ዛሬ ድረስ ለዘለቀው የመከራ ኑሮ የተዳረግንበት ጊዜ ነው። መስከረም አልፎ ሌላ መስከረም ቢተካ ለረጅም ጊዜ የምንመኘው በዋናነት ሰላምና አንድነት፣እድገትና የሕዝብ ጤናማ ግንኙነት እዬራቀን መሄዱን እንጂ መሻሻሉን አላዬንም።የመስከረማችን የተስፋ ጭላንጭሉ እዬጠፋ በጋው ክረምት ከሆነብን ቆይቷል።ሥልጣን ላይ ለተቀመጡት ለጥቂቶቹ አምባገነኖችና ለአጃቢ ጥቅመኞቹ ግን ክረምቱ ከበጋው፣ መስከረሙ ከሃምሌና ነሃሴው ወራት የተለዬ አይደለም።ለእነሱ ሁል ጊዜ መስከረማቸው ነው። ዘወትር አስረሽ ምችው የሚደልቁበት እንቁጣጣሻቸው ነው።ህጻን ቢታረድ፣አገር ብትበታተን ደንታቸው አይደለም። ከአገር እዬዘረፉ በውጭ አገር ያስቀመጡት ገንዘብ፣ የገዙት ቤትና ንብረት ስላላቸው አይሰጉም።ኮሽ ሲል ለመፈርጠጥ ሻንጣቸውን እንደሚከሽፉ አይተናል።ለነሱ አገርና

ክብራቸው ሆዳቸው ብቻ ነው።የመከራው ገፈት ቀማሽ ፣ መብቱ ተከብሮ ላልኖረባት አገር ላቡንና ደሙን እያፈሰሰ፣ሕይወቱን እዬገበረ የኖረው ብዙሃኑ አገር ወዳድ በተለይም የአማራው ተወላጅ ነው። ለዚህ ህዝብ መስከረሙ ከራቀው ቆይቷል።ሁል ጊዜም ቢሆን በጋው ክረምት ሆኖበታል።ከዚያ የጨለማ ወቅትና አገዛዝ ለመላቀቅ አሁንም የሞት የሽረት ትግል በማድረግ ላይ ነው።የማታ ማታ በድል አድራጊነት የብሩህ ተስፋ መጀመሪያ የሆነውን የመስከረም ወር ለማክበር የሚችልበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።መስከረሙን ሊያቀርበውና ሊያርቀው የሚችለው የሱ የትግል አቅጣጫና ቆራጥነት ነው። ጠላትና ወዳጁን ለይቶ የዓላማ ጽናት ኖሮት ሃይሉን አስተባብሮ ከተነሳ የማያልፈው ክረምት፣የመከራ ጊዜ አይኖርም።

ምኞት አይቀርምና የገና ወይም የክርስቶስን  የልደት በዓላችንን ተከትሎ ፣ሰላምና አንድነትን የሚያረጋግጥልን እውነተኛ ስር ነቀል  ለውጥ የሚወለድበት ጊዜ እንዲሆንልን የኢትዮጵያ አንድነት የራድዮ ስርጭት ምኞቱን እዬገለጸ ወዳሳለፍነው ሳምንት ዘገባና ትንታኔ እናመራለን።

ካለፈው ሰኞ ስንጀምር በባሕርዳር እስርቤት ውስጥ የሚገኘውን ፋኖ ዘመነ ካሴን በጉልበት ለመውሰድ እስር ቤቱን  መሣሪያ በታጠቁ  የኦነግ ብልጽግና አፋኝ ሃይሎች ከበባ የተደረገው ሙከራ በእስርቤቱ ጠባቂዎችና ታራሚ እስረኞች እንዲሁም ከያቅጣጫው በተሰበሰበው በከተማው ነዋሪ ሕዝብ በተለይም በወጣቱ እምቢባይነት ሳይሳካ ቀርቷል።ይህ ማለት ግን የመንግሥት ተብዬው የኦሮሙማው ተረኛ ቡድን ሙከራ አከተመለት ማለት አይደለም።በተለያዬ ጊዜና ስልት መሞከሩ አይቀርም።እንደሚሰማው ጭምጭምታማ ከሆነ የገዳይ ቡድን በእስር ቤቱ ሰርጎ ለማስገባት ሴራ መጠንሰሱ ይነገራል።በተገኘው ውጤት ተዝናንተው ሳይቀመጡ ይበልጥ ተደራጅቶ መጠበቅ አስፈላጊ ነው።የኦነግ ብልጽግና  ፍላጎት ከዘመነ ካሴ በላይ አገር የማፍረስ ዓላማ ነው።

የሕዝቡ ትግል አሸናፊነቱን በዚህ ብቻ ሳይሆን መተማ አካባቢ  በገንዳውሃ ታስረው የነበሩት አምስት የፋኖ አባላትም ለመለቀቅ ችለዋል።ሆኖም ግን ሥርዓቱ መልሶ ለማሰር ሲል አዲስ ወንጀል  ፈጥሮ ክስ ለመመስረት መንቀሳቀሱን  ሰምተናል።ከእስር የተለቀቁት በሰጡት መረጃ  በሰው ልጅ ላይ ሊደርስ በማይገባውና በአሳፋሪ ደረጃ፣ፍጹም ሲሰሙት የሚዘገንን ስቃይ በእስር ቤቱ ውስጥ  የተፈጸመባቸውና ትእዛዙም ከራሱ ከአብይ አህመድ እንደመጣ ገልጸዋል።  በመምህሪት መስከረም አበራና በአዛውንቱ ጋዜጠኛና የታሪክ ተመራማሪ በሆነው ታዲዎስ ታንቱ ላይ የተፈጸመውና፣ በጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ላይ የሚያንዣብበው አደጋ የዚያ ማረጋገጫዎች ናቸው።የጎሰኞቹ ስርዓት እስካለ ድረስ ይህ አይነቱ እኩይ ተግባር አይቆምም።ለጊዜው መስከረም አበራ በ50 ሽህ ብር ክፍያ ዋስትና መለቀቋ ቢገለጽም በውጭ ሆና እንድትከራከር እንጂ ከክሱ ነጻ አልሆነችም።ነገ መልሳ ላለመታሰሯ ዋስትና የለም።

በዚሁ ሰኞ ቀን በፍትህ ሚኒስትሩ በጢሞቲዎስ የሚመራ ቡድን በደብርሃን ከተማ  “ የመምህራን ሚና በአገር ግንባታ ላይ”በሚል ርእስ መምህራንን ሰብስቦ ለማነጋገር ያደረገው ሙከራ በመምህራኑ በኩል “መጀመሪያ ለመኖር የምንችልበት የደመወዝ ጥያቄያችን መልስ ይሰጠው፣በርሃብ እዬተሰቃዬንና በኑሮ ውድነት እዬተቃጠልን ስለ አገር ግንባታ የምናወራበት አቅምና ፍላጎት የለንም” በማለት የስብሰባ አዳራሹን እረግጠው በመውጣት ጢሞቲዎስን አሳፍረው መልሰውታል።ጢሞቲዎስ ለመምህራኑ የሰጠው መልስ መንግሥት ደመወዝ ሊጨምር አይችልም፣ዩኒቨርሲቲዎች ከመንግሥት ተላቀው ወደ ንግዱ ሥራ ገብተው፣እውቀት እዬሸጡ  የመምህራኑን ጥያቄ ለመመለስ የራሳቸውን የገቢ ምንጭ መፍጠር አለባቸው የሚል ነበር።አብይ አህመድም ይህንኑ ቀደም ሲል ገልጾታል፤እኛም እንደ ኢትዮጵያ ባለ ደሃ ሕዝብ በሚኖርባት አገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የግል ይሁኑና ይከፈልባቸው ማለት ደሃ አይማር፣ብሎ እንደመፍረድ ይቆጠራል በማለት የ1966ቱን የሴክተር ሪቪው እቅድ ያመጣውን ቀውስ ለማስረጃነት አቅርበን ነበር።

በቀጣዩ ማክሰኞም የአንበሳ አውቶብስ አገልግሎት ሠራተኞች በዬዓመቱ ይደረግ የነበረው የደረጃ እድገትና  የደመወዝ ጭማሪ ላለፉት ሁለት ዓመታት ባለመደረጉ ደንቡ እንዲከበርላቸው የጠዬቁት ጥያቄ በፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ የተላለፈው ውሳኔ ተግባራዊ ባለመሆኑ የሥራ አድማ ለማድረግ መንቀሳቀስ መጀመራቸውን የገለጹበት እለት ነበር።ሠራተኞቹ እስከ ታህሳስ 27 ቀን ድረስ መልስ ካላገኙ የሥራ ማቆም አድማ እንደሚመቱ አስጠንቅቀው ነበር። የቤት ሠራተኛ ከሶስት ሽህ ብር በላይ በሆነበት፣የቤት ኪራይና የልጅ ትምህርት ቤት ክፍያ ከአቅም በላይ በሆነበት፣በቀን አንድ ጊዜ እንኳን በልቶ ለማደር ባልተቻለበት ጊዜ ከአስራ ሁለት ሰዓት በላይ በሥራ ተጠምደን  ማግኘት የሚገባንን ማጣታችን  እንደ ዜጎች ብቻ ሳይሆን እንደ ሰው መቆጠራችን አጠራጥሮናል ሲሉ ብሶታቸውን በምሬት ገልጸዋል።እኛም ብሶታቸውን እንጋራለን።የመሥሪያ ቤቱ ሃላፊዎች ከመጠን በላይ ደመወዝ ሲከፈላቸው፣በባለሥልጣናቱ የቀን አበል ብቻ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በሚባክንባት አገር የሰፊው ሠራተኛ ሕዝብ ኑሮ ከድህነት ወለል በታች መሆኑ ልብ ይሰብራል።ጨዋ ሕዝብ በመሆኑ እንጂ የጉዳቱ መጠን በአስተዳዳሪዎቹ ላይ ከባድ ጉዳት ባደረሰም ነበር።አሁንም ጥያቄያቸው ካልተመለሰ ከፍተኛ እርምጃ እንደሚወስዱ ከአነሳሳቸው መገመት ይቻላል።እንደሌሎቹ የሕዝብ ትግሎች  ይህም የአንበሳ አውቶብስ ሠራተኞች ትግል በሰርጎ ገቦችና ስርዓቱ ባስማራቸው የኦሮሙማ ተረኝነት ስሜት በሚነዳቸው የውስጥ አርበኞች እንዳይደናቀፍ ብሎም የትግል መሪዎቹ ለበለጠ ጉዳት እንዳይጋለጡ ስጋታችን ነው።ለጥያቄያቸው መልስ ይሰጥ አይሰጥ የታወቀ ነገር የለም።ለሃሙስ የያዙት ቀነ ገደብ በማለፉ አድማ  የመምታታቸው ውሳኔ ዛቻ ብቻ የሆነ ይመስላል።ግን ይዋር ይደር እንጂ የታሰበ ነገር ጊዜውን ጠብቆ መፈንዳቱ አይቀርም።

በዚሁ ማክሰኞ እለት የተረኛው የኦሮሙማው አስተዳደር አዲስ አበባን የመዋጡን ሂደት በማስቀጠል ለዘመናት የኖሩትን የሌላውን ጎሳ ተወላጆች በተለይም የአማራውን፣የጉራጌውንና ሌላውን ኦሮሞ ያልሆነውን  ማህበረሰብ እዬነጠለ መኖሪያ ቤቱን በማፍረስ ላይ የተጠመደበትና ነዋሪው ባላሰበው ሰዓት ሌሊት ላይ በአፍራሽ ሃይል ቤቱ ተንዶና ፈራርሶ እቃው ወድሞ ሜዳ ላይ ፈሶ ጨኽቱን የሰማንበትና የታዘብንበት ቀን ነው።በአንድ ቦታ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ቦታዎች ማለትም  ለቡ ገብርኤል ወይም ለቡ ባቡር ጣቢያ፣ኮልፌ ቀራንዮ፣አሸዋ ሜዳ፣ግራር ሰፈር፣ገሙ፣ቡራዩ በተባሉት የከተማው ጠርዝ አካባቢዎች በተወሰደው ጸረ ሕዝብ እርምጃ ህጻናት፣አሮጊትና ሽማግሌዎች ፣አራስ እናቶች ሳይቀሩ ሜዳ ላይ ፈሰዋል።በዚህ ፋሽስታዊ እርምጃ  የኦሮሙማው ልዩ ሃይል በመሳተፉ ባልታጠቁ ንጹሃን ላይ በከፈተው ተኩስ ከአምስት ሰዎች በላይየሞቱ ሲሆን ብዙዎችም የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል።አሁንም የቤት ማፍረሱ እርምጃ ተጠናክሮ ቀጥሏል።ያንን ለማድበስበስ አዳነች አቤቤ ለአድርባይ የኪነት ሰዎች የከተማ ቦታ ካርታና የቤት ቁልፍ ስታድል ሰንብታለች።

ባለፉት ቀናት የታዩት ሕዝባዊ ተቃውሞዎችና ጥያቄዎች ለዳግማዊ የካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዋዜማዎች ይመስላሉ።የሕዝባዊ ትግሉ ጽንስ አዋላጅ ይፈልጋል።እንደ ቀዳሚው የዬካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንዳይጠለፍና እንዳይጨነግፍ ከዚህ ቀደም ደግመን ደጋግመን እንዳሳሰብነው ትግሉን የሚያስተባብርና የሚያስተሳስር አንድ አካል ይፈጠር የሚለው የዛሬውም መልእክታችን ነው።አሁን ሁኔታው ከቀድሞው የካቲት በላይ ነው።የአገር ህልውና፣የመኖርና አለመኖር ጥያቄ ነው።አገር አፍራሾች ሥልጣኑን ጨብጠው  ለመበታተን ያሻቸውን የሚያደርጉበት ጊዜ ላይ ነን።ወያኔና ኦነግ ብልጽግና የጋራ ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ የሚሊዮን ሕዝብ ህይወት ካስጠፉበት ጦርነት ወጥተው ለዘላቂ ዓላማቸው በአንድ ላይ የቆሙበት ወቅት ነው።ሰልፉ ለይቷል፤ይፋ ወጥቷል።አብይ አህመድ በሚመራው የኦሮሙማ ተረኛ ቡድን የአማራው ልዩ ሃይል ፋኖና ሚሊሽያ እንዲሁም ነዋሪው ሕዝብ ከራሱ አጽመ እርስቶች ከወልቃይትና ጠገሌ፣ከራያና ቆቦ ፣ለቆ እንዲወጣ ተፈርዶበታል።ዙሪያው በወያኔ ጦር ተከቧል፤ከውስጥም የኦነግ ጦር በመከላከያ ስም ሰርጎ ገብቷል።ትግሉ መሪር ነው።ለአገር

አንድነትና ለዜጎች መብትና ክብር የሚታገል ሁሉ ሥርዓቱን በቃላት  ከማውገዝ ባለፈ በወሳኙ ትግል ላይ እንዲሳተፍ ጥሪ እናደርጋለን።ይህ ማለት ግን አሰሱ ገሰሱ፣እቶ ፈንቶው፣ያይተነው ጊዜ ሰልፈኛ ገብቶ ያቧችርበት ማለታችን አይደለም።

የሕዝቡን ትግል ለማጨናገፍ በማስተባበር ስም የሥርዓቱ አጃቢዎችና የአብይ አህመድ ጫማ ላሾች የተሰበሰቡበት ግሎባል አሊያንስ(Glabal Alliance) በሚል ስም ገንዘብ ሲዘርፍ የኖረው የግንቦት ሰባቶቹ ቡድን አሁን ደግሞ ዓይኑን በጨው አጥቦ  ትግሉን ፈር ለማስለቀቅ አስተባባሪ በሚል ስም ብቅ ብሏል።ወግድ ሊባል ይገባል።አካፋን አካፋ ማለት ተገቢ ነው።ሃይልን ማሰባሰብ በሚል ሞኝነት እንዲህ አይነቱን ያድር ባዮች ስብስብ አቅፎ መሄድ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።ሌላው ቀርቶ ለፈጸሙት ያድርባይነትና ክህደት ተግባር የእምነት ቃላቸውን አልሰጡም፤ይቅርታም አልጠዬቁም።ይህንንም ቢያደርጉ አርፈው እንዲቀመጡ ይፈቀድላቸዋል እንጂ ትግሉ ውስጥ ገብተው ያውም በአስተባባሪነት ቦታ ላይ ተቀምጠው እንዲያቦኩ መፍቀድ ትልቅ ስህተት ይሆናል።ትግሉ ይጥራ ፣ወዳጅና ጠላት ይለይ የምንለውም ለዚያ ነው።

የሥርዓቱ ተጠሪዎች የሚይዙ የሚጨብጡትን አጥተዋል። በስብሰባ ተጠምደዋል።አንዱ ስብሰባ ሳይጠናቀቅ ሌላ ስብሰባ በመጥራት ላይ ናቸው።የደማ ወይም የቆሰለ ነብር ሃይሉን የሚጠቀመው ተስፋ በቆረጠበት ጊዜ ነው ይባላል።ይህም የጎሰኞች አውሬ ስብስብ ያሰበው ሳይሳካለት በመቅረቱ ይመስላል ሁሉንም እንዳበደ ውሻ መንከሱን መርጧል።የአገር አፍራሾቹን ጎራ በገንዘብ፣በዲፕሎማሲና በፖለቲካ የሚረዳው የአውሮፓ ህብረትም እንደ አንዱ አህጉራዊ ጥያቄ አድርጎ በወያኔና በኦነግ ብልጽግና መካከል የተደረገውን ስምምነት አካሄድ ለመመርመር በሚል ሽፋን ስብሰባ ለማድረግ ወስኗል።

የአገር ወዳዱ ትግል እያደገና ምህዳሩ እዬሰፋ ሲመጣ ፈሩን ለማስለቀቅና ትኩረት ለማሳጣት የኦነግ ብልጽግና ጎራ ደጋፊ የሆኑት በአሜሪካ የሚኖሩ ነጋዴዎች አሜሪካ ከዓመት በፊት ያገደችውን የአጎዋ(AGOA) የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚነት መልሳ እንድታነሳ ሲሉ ደብዳቤ ለባይደን መንግሥት ለመጻፍ ማሰባቸውን ይፋ አድርገዋል።ይህ ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ ጥቅም ይገኝበታል የተባለው የነጻ ንግድ ዝውውር ፈቃድ የሁለት  መቶ ሽህ(200,000) ሠራተኞችን የእለት ኑሮ የሚሸፍን፣ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ነው በሚል ሽፋን የጥቂት ባለሃብቶችን ጥቅም በደሃው  ስም የማስጠበቅ ዘዴ እንደሆነ አይካድም።በእኛ አስተሳሰብ ልብስና ጌጣጌጥ እንዲሁም ፍራፍሬና አበባ  እያመረቱ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት የቻይና፣የቱርክ፣የህንድ፣የኔዘርላንድ፣የሳውዲ---ወዘተ ኩባንያዎች  የጥቅም ተካፋይ ከሆኑት ባለሥልጣኖች ጋር በመተባበር ስለሆነ የአገር ንግድ ተደርጎ መቆጠር የለበትም። ገንዘቡ በያገራቱ ባንክ ውስጥ ይቀራል እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የሚውል አይሆንም።የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ማለት አንዱ ገጹ በኤኮኖሚ ዙሪያ የበላይነትን ማግኘት ሲሆን ያም ለፖለቲካው የበላይነት የሚረዳ ዋና ሞተር ነው።

የአንድ አገር አምራች ድርጅት ለውጩ ገበያ ከማቅረብ በፊት ያገር ውስጥ ፍላጎቶችን የማሟላት ሃላፊነት አለበት።እንዲያ ከሆነ ደግሞ ለውጭ አገር ልብስና ጌጣጌጥ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ያድነዋል ፣ከዚያም አልፎ ተርፎ የአገርን ኤኮኖሚ በማሳደግና እራስን በራስ የመቻሉን አቅም ይገነባል፣ ጥገኝነትን ያሶግዳል፣ለተራቀቀ ሥራና ሙያ ያበቃል እንላለን። ከውጩ ንግድ ጋር መተሳሰር የለብንም አንልም።ለዶላርና ለኤሮ ሲሉ ብዙ የመጓጓዣ ወጭ ከማውጣት ይልቅ  የቅርብ ገበያ በመፍጠር ለአፍሪካ አገሮች ቢሸጥ ጥቅሙ የጎላ ይሆናል፤ለፓን አፍሪካንዝም መርሆም ማጠናከሪያ ይረዳል። በመአድንና የተፈጥሮ ሃብት ዙሪያ የምንጠቀምበትን ተጠቅመን የተረፈንን ብንሸጥ ለሚያስፈልገን መግዣ ማዋሉ ትክክልና ተገቢ መሆኑን አንክድም።የምንቃወመው የተገላቢጦሽ የሆነውን፣የጥቂቶች

መጠቀሚያ፣የዘረፋና ብዝበዛን ፣ የተዛባ፣የጌታና የባሪያ ግንኙነት መኖሩን ነው።በእኛ ኪሳራ ሌላው መጠቀሙን ነው።

አሜሪካኖች ጎዋን ሲፈቅዱ ለአፍሪካ ደሃ ሕዝብ አስበውና ተጨንቀው ሳይሆን የማሰሪያ ገመድ ሊሆናቸው እንደሚችል በመረዳት ነው።በጎዋ ገበያ ስም የሚገኘው ገንዘብም በራሳቸው ባንክ ውስጥ እንደሚቀርና እንደሚሽከረከር ያውቁታል።የግሎባላይዜሽን አንዱ መገለጫ እንዲህ አይነቱ ወጥመድ ነው።

ሌላው ዓይን ያወጣው የአሜሪካኖቹ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ተጽእኖ ገደቡን አልፎ በወታደር ሃይል መታጀቡን ሰምተናል።በኢትዮጵያ፣በኤርትራ፣በሶማሊያ፣በጅቡቲ በአጠቃላይ በአፍሪካ ቀንድ አገሮች ወታደር በመላክ ሰላም ለማስከበር በሚል ሽፋን ጥቅሟን ለማስከበር መነሳቷን ይፋ አድርጋለች።ይህ መሆን ከጀመረ የቆዬ ቢሆንም አሁን ወሳኝ ደረጃ ላይ በመድረሱ ይፋ ሆኗል።በሶሪያ፣ በሊቢያ፣በየመን፣ በአፍጋኒስታን፣በዩክሬን ጦርነትን የቀሰቀሱት እነሱ መሆናቸው ሲታወቀ አሁን በአገራችን መግባታቸው የቀውሱን ደረጃ ከፍ እንደሚያደርገው አንጠራጠርም።ሌላው ቢቀር ኤርትራ እንገባለን ሲሉ እውነት ለኤርትራ ሕዝብ ሰላም አስበው ነው የሚል ጅል ይኖራል ብለን አናስብም።ዓላማቸው ግልጽ ነው ከወያኔ ጋር ተባብረው ያስቸገራቸውን ኢሳያስ አፈወርቂንና አገዛዙን አሶግዶ በምትኩ ባንዳና አድርባይ አገዛዝ ለማስቀመጥ ነው።የአሜሪካኖቹ በከባቢው ወታደራዊ ሃይል ማሰለፍ ከባቢውን ለበለጠ ቀውስና ቋሚ ጦርነት ይዳርጋል እንጂ ሰላም አያመጣም።ለተንጠለጠለው የሶስተኛው ዓለም ጦርነት ስጋት የቀድሞ ምሽግ ቦታ ቁፋሮ ጋር የተያያዘ ነው እንላለን።

አብይ አህመድ የሚመራው የተረኛው ኦነግ ብልጽግና አገዛዝ የሕዝቡን ትኩረት ለማስቀዬር የማይገለብጠው ድንጋይ የለም።አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ የራሷን ሶስተኛውን ሳተላይት ለማምጠቅ ዝግጅት ላይ ነች የሚል ወሬ ይዞ ብቅ ብሏል። መቸም እንደ ዜጋ አገራችን ለዚህ ደረጃ እውነት ብትበቃ ኖሮ ደስታችን የላቀ ይሆን ነበር።ዳቦ ጠፍቶ ፣ሰላም ጠፍቶ፣ሕዝብ በስቃይ በሚኖርባት አገር፣ ሕጻን የመኖር ብቻ ሳይሆን የመወለድ መብቱን ተገፎ ከማህጸን ተጎትቶ በሚጣልባት አገር ውስጥ ሆኖ በውጭ አገር ኩባንያ፣በቻይናዎች የተሠራ ሳተላይት ገዝቶ ማምጠቅ ከእብደት እኩል ይቆጠራል እንጂ የእድገትና የመሻሻል ምልክት ተደርጎ መወሰድ አይኖርበትም።የቅደም ተከተል መርሆን ያላገናዘበ ለገዢው ቡድን ወንጀል ሽፋን የሚሰጥ ሙከራ ነው።መጀመሪያ በአገር ውስጥ በሥርዓቱ ተሰርቶ እንደ ሮኬት ተምዘግዝጎ የወጣውን የኑሮ ውድነትና የሰላም እጦት ፣የጎሰኝነትና የተረኝነት ወረርሽኝ ማጥፋቱ ይቅደም እንላለን። እዬዬም ሲደላ ነው!

የአዲስ አበባው የኦነግ አስተዳደር የሕዝቡን ትኩረት ለማስቀዬር ሲል በቀን ከ250,000 ሽ በላይ እንጀራ የሚጋገርበት ፋብሪካ መክፈቱን ይፋ አድርጓል።ቀደም ሲል ይኸው የከተማ ተረኛው አስተዳደር ሁለት ሚሊዮን ዳቦ በቀን የሚጋግር ፋብሪካ መክፈቱን ይፋ አድርጎ ነበር።ሆኖም ግን ዳቦው በስሎ ሳይበላ ሊጥ ሆኖ ቀርቷል።የእንጀራውም ነገር ከዚያ የተለዬ አይሆንም።መጀመሪያ ሰላምና የእህል ምርት መኖሩ ወሳኝ ነው።የልመና እህል እያሳደዱ፣በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በርሃብ እዬተሰቃዬና እየሞተ፣በደሃው ሕዝብ ምድጃ ምጣድ ላይ የሚጋገር በጠፋበት ወቅት በፋብሪካ ደረጃ አዘጋጅቶ ለገበያ አቀርባለሁ ማለት የሕልም እንጀራ ከመሆን አያልፍም።ቢጋገርም ለቅንጡዎቹ እንጂ ለደሃው ሕዝብ አይተርፍም።

እሮብ ታህሳስ 26 ቀን አማራ ክልል በተባለው የጎሳ ሥርዓቱ እስር ቤት፣የብልጽግና አገዛዝ የተነሳበትን ሕዝባዊ አመጽ ለማስቆም የመሪዎች ስብሰባ መጥራቱ የሚታወቅ ነው።በዚህ ስብሰባ ላይ ከበላይ እስከታችኛው እርከን በሃላፊነት የተመደቡ ከ3500 በላይ የሆኑ የሥርዓቱ ሹመኞች እንዲሰበሰቡ

ሲደረግ በጣም የሚያሳዝነውና የሚያሳፍረው ስብሰባውን በበላይነት እንዲቆጣጠር የመድረኩ መሪነት የተሰጠው የኦሮሙማው አገረገዢ የሆነው ሽመልስ አብዲሳ መሆኑ ነው። ከዚህ በላይ ለአማራው ማህበረሰብ ሞት የለም። ሽመልስ አብዲሳ የተባለ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አማራ ግለሰብ በሚያስተዳድረው ክልል በአማራው ላይ ለሚደርሰው ግፍና መከራ፣እልቂትና መፈናቀል ዋና አስተባባሪና መሪ የሆነን ወንጀለኛ ስብሰባውን እንዲመራ ማድረጉ የብአዴን መሪዎች እውነትም አሽከሮች መሆናቸውን ያረጋገጡበት ተጨማሪ ድርጊት ነው።ከበላይ ምስለኔዎች ይልቅ በዝቅተኛ እርከን ላይ የተቀመጡት በመሻል ሽመልስ አብዲሳንና የብአዴንን ከፍተኛ አመራሮች በጥያቄ ማፋጠጣቸውን ሰምተናል።ይህንን የውስጥ ቅራኔ የቀሰቀሰው የሕዝቡ ትግል እንደሆነ አይካድም። በሥርዓቱ ውስጥ ያሉት የሕዝቡን ትግል ለመቀላቀል የቆረጡ መሆናቸው በቀጣዩ የሚታይ ይሆናል። የሥርዓቱ ቁንጮዎች ይህንን ውስጣዊ ተቃውሞ በሃይል ለመደፍጠጥ እንደሚንቀሳቀሱ እርግጠኞች ነን።ግን ትግሉን ያባብሰዋል እንጂ ሊገታው አይችልም።ሆነም ቀረም ፣ለተቃዋሚዎቹም የሚያዋጣው መንገድ ከአቋማቸው ሳያፈገፍጉ ከሕዝቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ ነው።የሕዝቡ ትግል ውጤታማም እንዲሆን በተመደቡበት ቦታ ሁሉ ሕዝባዊ ኮሚቴ፣የለውጥ ሃይል እንዲደራጅ ማገዝና ማበረታታ ነው።በዬቦታው የሚንቀሳቀሱትን የሕዝብ ኮሚቴዎች የሚያስተሳስር አንድ ማእከል መፍጠር የግድ ይላል።ያ ከተሟላ ለስር ነቀል ለውጥ አዳጋች አይሆንም።

የራያና ቆቦን፣የወልቃይት ጠገዴና ጸለምትን መሬት ከአማራው ነጥቆ ለወያኔ የመስጠቱ ውሳኔ ለመጭው ወሳኝ ሕዝባዊ ትግል መንስኤ እንደሚሆን አንጠራጠርም።የአማራው ፋኖ እራሱን በማሰባሰብና በማደራጀት ላይ ሲሆን የገዢው የኦነግ ቡድን ከወያኔ ወራሪ ሃይል ጋር በማበር ወረራ ለማካሄድ በመዘጋጀት ላይ ነው።ከዚያም አልፎ በክልሉ የሚታዘዘው ልዩ ሃይል የያዘውን ቦታ ጥሎ እንዲወጣ ተደርጓል።ይህ የመንግሥት ቀለብተኛ የሆነ ሃይል በቀጣዩ ከራሱ ከአማራው ፋኖ ወገኑ ጋር ጦርነት እንዲገጥም ሳይገደድ አይቀርምና ያ ከመሆኑ በፊት ለጠላት መሣሪያ ሆኖ በራሱ ላይ እንዳይዘምት እንዲያስብበት ጥሪ እናደርጋለን።ሌላውም በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በተለይም የአማራው ተወላጅ ተባብሮ ሕዝባዊ ትግሉን በሚቻለው መጠን እንዲረዳ ጥሪ እናደርጋለን።የአማራው መዳን የኢትዮጵያ መዳን እንደሆነ ሁሉም አገር ወዳድ ሊያውቀው ይገባል።

ይህ በእንዲህ እያለ የአዲስ አበባው የኦነግ ብልጽግና ቡድን የቀድሞ ጌታውን የወያኔን ቡድን ለመቀበል የናጠጠ ድግስ ለማዘጋጀት ሽርጉድ በማለት ላይ ተጠምዷል።አድርባይ ዘራፊ ከበርቴዎች ወጩን እንዲሸፍኑ ትእዛዝ የተሰጣቸው ሲሆን ሆድ አደር የአማራው ከበርቴዎች ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። ህጻን ልጅ እናቱ እሬሳ ላይ ሆኖ ደረቅ ጡት ነክሶ በሚያለቅስበት፣በገንዘብ የማይተመን የሰው ልጅ ህይወት በጨካኞች እጅ በሚጠፋበት፣ ደም እንደ ውሃ በሚፈስባት አገር የፈረንሳይ ውድ ኮኛክና የአይረላንድ ውስኪ የተሞላ ብርጭቆ እያጋጩ መፈንጠዝ በፕላኔታችን ላይ በአረመኔዎች አገዛዝ ከታዩ ጭካኔዎች ሁሉ ተወዳዳሪ የሌለው ነው ለማለት እንደፍራለን።ከድግሱ ማግሥት የሥልጣን እርክክቡ እንደሚቀጥል ታውቋል።ከጦርነቱ በፊት ገና ከጅምሩ የተጣሉት በሥልጣንና በጥቅም መሆኑንና የሚታረቁትም በዚሁ ሲሆን እንደሚችል መግለጻችን አይረሳም።አሁንም ያዬነው ይህንኑ ሲሆን ወደፊት የሚጣሉበት ነገር ቢኖርም ከዚህ አይለይም።የትግራይ፣የአማራውና የአፋሩ ሕዝብ ለነዚህ አውሬዎች ጭዳ መሆኑ ያሳዝናል፤ይበልጥ የሚያሳዝነው ግን ሕዝቡ ሰላም ወረደ በሚል አዚም ውስጥ ገብቶ ለነዚህ ጨካኞች መጠቀሚያ መሆኑ ሲሆን ለደረሰበት ውድመትና እልቂት ተጠያቂ ናችሁ ብሎ በሕግ እንዲቀርቡ ብሎ አለመጠዬቁ ነው።በኢትዮጵያ ጉዳይ የውጮቹ በተለይም አሜሪካኖቹና አውሮፓውያኑ ወሳኞች፣ አድራጊ ፈጣሪ መሆናቸው ደግሞ ሌላኛው አሳፋሪ ጉድ ነው።እነሱም የድግሱ ተቋዳሽ ለመሆን በቦታው ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ይህ ሁሉ የሚሆነው የኑሮ ውድነት ቀስፎ በያዛት አገራችን ውስጥ ነው።በትናትናው የገና በዓል ገበያ ላይ የታዬው የዋጋ ግሽበት ከመቼውም ጊዜ የከፋ ሆኖ ተገኝቷል።ዶሮ  እስከ 1,300 ብር፣የበግና የፍዬል ሙክት እስከ 30,000ሽ ብር ፣በሬ እስከ 60,000ሽ ብር ድረስ ማውጣቱን፣ በጥቁር ገበያው አንዱ ዶላር እስከ 105 ብር መድረሱ ብቻ ሳይሆን በግልጽ በመንገዶች ዳርቻ መካሄዱን ሰምተናል።ብዙ ሽህ ዶላር ያለውም እስከ 113 ብር ተመን ድረስ  ሊመነዝር ይችላል።ይህ ሁሉ ሲደመር ያገራችን የነገው ጉዞዋ ከፖለቲካው ቀውስ ጋር ተያይዞ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ሲገምቱት ይዘገንናል።ቀውሱ ባይቀርም ለመቀነስ የትግሉን አቅጣጫ የሚቀይስና ሕዝቡን የሚመራ አካል መፍጠር ለነገ የማይሉት ተግባር ነው።ትግላችን የውስጡን ብቻ ሳይሆን የውጭ ሃይሎችንም ጣልቃ ገብነት የሚከላከልና የሚያመክን መሆን አለበት። ያም ትግሉን መራራና አዳጋች ያደርገዋል እንጂ የማታ ማታ ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው።የቬትናሞችን፣በቅርቡም ምንም እንኳን ኋላቀር ለሆነ የታሊባኖች አገዛዝ ቢዳርግም የውጭ ሃይሎችን አሳፍሮ የመለሰውን  የአፍጋኒስታኖችን ውጤት ማዬቱ ይበቃል።

ሕዝባዊ ትግሉ ይፋፋም!! የጋራ ግንባር ይመሥረት!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!